ህዳር 4/2004 ዓ. ም.

በአዶላ ወዩ ተዘጋጀ

ይህ ግጥም ለ-ኢህአፓ የ 39ኛዉ ምስረታ በአል የተበረከተ ነዉ

አለብህ አደራ

በለኝ ልበልሃ

የጥንቱን ያባቴን ልንገርሃ

የያኔዉን የዱሮ የዱሮዉን

የባለፈዉ የቀድሞ የጥዋቱን

የኢትዮጵያዊነት መሰረቱ ኩራቱ

አንድነት ነበር ዋናዉ ምልክቱ

ጀግንነት ነበር መታወቂያነቱ

ለደስታም ሆነ ለመከራ

ለሀዘን ለለቅሶ ለጭፈራ

ሁሉም በየቁዬዉ ተጠራርቶ

ያዘነን አጽናንቶ

አብሮ ጠጥቶ አብሮ በልቶ

ይኖር ነበር ወገን ተከባብሮ

በሽምግልና በአዉጫጭኝ ተመካክሮ፡፡

የተጣላን አስታርቆ የታመመን ጠይቆ

ዘር ሃይማኖት ሳይል በጋራ

ጠላት ሲመጣ እየተጠራራ

እምቢኝ ብሎ ለሃገሬ

ወገን ተሰባስቦ ከየጎሬ

ያሳየዉ ነበረ ጠላትን አበሳ

ምስክር ይሁነኝ ያ መይሳዉ ካሳ

አንተ ወጣት ትውልድ አለብህ አደራ

አገር ለመጠበቅ አንድ ሁንህ በጋራ

ጎበዝ ተነሳ እንጂ ምነዉ መተኛትህ

አገርህ ስትሸጥ አድፍጠህ ማየትህ

በአንድ ላይ ሆነን ተነስ እንነሳ

ከወያኔ ቀንበር ኢትዮጵያን እናንሳ

በገዛ አገርህ ሳትሆን ስደተኛ

እንቅልፍ እንዳይዝህ ተነስ አትተኛ

ተሰለፍ ግባና ከ-ወክንድ ጎራ

ተሰለፍ ግባና ከኢህአፓ ጋራ

ወያኔን እናጥፋዉ አንድ ሆነን በጋራ

ወያኔ የሚሉት ቫይረስ መጥቶብን

ኢትዮጵያዊነቱን ዘንግቶ ጭርሱን

ታላቂቱን ትግራይ ሊገነባ አስቦ

መሬት ተሰሜኑ ወደ ምስራቅ ከፍሎ

ኢትዮጵያን ሊያጠፋ **<u>ተገዝቶ</u>** ምሎ (ገ ይጠብቃል) መገዘት

ከደቡብ ከምእራብ የህዝብ ንብረት ዘርፎ

ኢትዮጵያን ለማዳን ከወያኔ ሴራ

ስማኝ ያገሬ ልጅ እንዳይቆጭህ ሑዋላ

መቀበሪያ አጥተህ በወያኔ በላ

እሬሳህ ተጥሎ ባዉሬ እንዳይበላ

መሬት ተሸንሽኖ ተሸጦ ለባዳ

ወገን ተፈናቁሎ ወድቆ በየሜዳ

ሀገሬ ኢትዮጵያ የባህር በር አጥታ

እንዳትበታተን የማታ የማታ

በዘር በሃይማኖት ህዝቡ ተከፋፍሎ

ነብሰ ገዳዮችን ባንተ ላይ መልምሎ

በነብስ አባቱ ስም በጳውሎስ ስም ምሎ

በሰበብ አስባቡ ሽብርተኛ ብሎ

ቃል ገብቶኣል ወያኔ በአቡነ ዲያብሎስ

ኢትዮጵያን ሊያጠፋ ህዝቡን ለማስጨርስ

በገዛ አገርህ ነጻነት ተነፍገህ

ቤቱም ያንተ አይደለ መሬት ተከልክለህ

ለልጅ የምትሰጠዉ ምታወርሰዉ የለህ

እንዴት በዝምታ ቁጭ ብለህ ታያለህ

ከአለሙ ካርታ ላይ ኢትዮጵያ ተፍቃ

አገር ልትጠፋ ነዉ ከምድረ አፍሪቃ

ተነሳ ወገኔ መተኛቱ ይብቃ

ወገን እንነሳ ባንድነት ሆነን

በዘር በሃይማኖት መበታተን ትተን

አንድ አላማ ይዘን ሆ ብለን ተነስተን

ወያኔን እናጥፋ ከነ ነብስ አባቱ

ተነሳ ወገኔ ጎልማሳ ወጣቱ

ኢትዮጵያን ለማዳን አሁን ነዉ ሰአቱ

ከዉርደት እናድን ኢትዮጵያን አማማ

ኻላ እንዳትቆጭ ከሰማኸኝ ስማ